# “አፐረሽን እንቁጣጣሽ!” ምስጢራዊው የስለላው ጦርነት!

## በኤርትራዊያን እይታ!

### ትርጉም ጌታቸው ረዳ

(Editor Ethiopian Semay getachre@aol.com)

ለዛሬ የምንመለከተው ጉዳይ ምስጢራዊው የስለላው ጦርነት (ስውር ስለያዊ ኲናት) በሚል ርዕስ ስሙ ያልጠቀሰ ኤርትራ ውስጥ “በአገራዊ የደህንነት ጽ/ቤት” አባል ከሆነ አንድ ኤርትራዊ፤ የሞላ ኣስገዶምና የወያኔ የስለላ መዋቅር በኤርትራ አስመልክቶ በትግርኛ ያሰራጨው ጽሑፍ ወደ አማርኛ የተረጎምኩትን እንመለከታለን።

“ድምህት” ሊቀመንበር የነበረው ሞላ አስገዶም ወደ 1500 ( ከሌኒን/ ከኮለኔል ፍፁም ስታፍ/አባሎች አንደበት መሰረት፣

በተነገረን መረጃ መሰረት ይላል መረጃ አቅራቢው) የሚገመቱ ወታደሮች ይዞ የኤርትራን ድምበር ጥሶ በሱዳን በኩል ወደ ኢትዮጵያ እንደተሻገረ መረጃው ደረሰን። ይላል ጸሐፊው።

ኤርትራ ውስጥ በሕዝብ ደህንነት ክፍል የሚሰራው ይህ ስሙን እንዲታቀብለት የገለጸው ጸሐፊ ያሰራጨው ጽሑፍ፤ ኣሰና በተባለው ራዲዮ ጣቢያ ለራዲዮው አድማጮች ተነብቧል።

የጽሑፉም ይዘት እንዲህ ይላል፡-

"በድምህት መሪው በሞላ አስገዶም መሪነት የተከናወነው ይህ አስገራሚ ወታደራዊ ፍጻሜ፤ በተለይም ከተጠቀሱት ወታደሮች መሃል ውስጥ በኢሳያስ ልዩ ትዕዛዝ ወደ ኢትዮጵያ አስሰርጎ ወያኔን ለመምታት ለልዩ ስልጠና ከላካቸው፤ የ4 ወር ስልጠና አጠናቅቀው በተመረቁበት ያኔውኑ ዕለት እነዚያ 400ዎቹ ልዩ ኮማንዶ ሃይል ከማሰልጠኛ ጣቢያ ይዟቸው በተቀናጀ ባስገራሚ መልኩ የኤርትራን ድምበር ጥሶ ወደ ኢትዮጵያ እንዴት ሊገባ ቻለ?"

" ..... ኤርትራ ውስጥ መንግሥታችን ብለን በምንጠራው በጎ ፈቃድ ተደራጅተው፤ ሎጅስቲካዊና የምክር እገዛ ተደርጎላቸው፤በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ሲሳተፉ ከ14 አመታት በላይ የቆዩት ዲሞክራሲያዊ ምንቅስቓስ ህዝቢ ትግራይ/ "ድምህት" በመባል የሚጠራው የኢትዮጵያ መንግሥት

ተቃዋሚ የነበረው የድርጅቱ መሪ በቅዱስ ዮሓንስ ዋዜማ ዕለት በ9/12/2015 (በፈረንጅኛው ዘመን ስለሚቆጥሩ) ከጉልጅ፤አም ሓጀርና ሐራና ተነስተው፤ ሙሉ ወታደራዊ ትጥቃቸው እንደያዙ የኤርትራን ድምበር ጥሰው ወደ አገራቸው ተመልሰው ገብተዋል።

ለብዙ አመታት በመንግሥታችን የታነፀው የድምህት ድርጅት፤ ድምበሩን ጥሶ ወደ ኢትዮጵያ መግባቱን ዜናው ከተሰማ በኋላ ፕረዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ልክ እሳተ ጎመራ ተለብልቦ እንደተሸረሸረው የራፋዕለ ድንጋይ (ኣፋር አካባቢ ነው) ተፍረክርኮ፤ ሆዱ ውሃ ቋጥሮ ተስፋው ሁሉ ባዶ ሆኖ ቀረ።

ኤርትራ ውስጥ በኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች መሃል ጥምረት ተከናወነ በተባለና ወዲያውኑ በተደረገው ጥምረትም ሞላ አስገዶም፤ 'የአገር አድኑ' ጥምርት ንቅናቄ ምክትል ሃላፊ ተብሎ ከተሰየመ በሓላ፤ በቅዱስ ዮሐንስ ዋዜማ ዕለት ወደ 1500 የሚያክሉ የታጠቁ ተዋጊ ሰራዊት ሃይል ይዞ የኤርትራን ድምበር በጥሶ በተለያዩ ድምበሮች እንደወጣ ደምህትና መሰል ተቃዋሚዎችን በቅርብ ከሚቆጣጠራቸው የኮለኔል ሌኒን ስታፍ/አባሎች ወሬው ደረሰን።

እነኚህ ተዋጊ ሃይሎች በፕረዚዳንት ኢሳያስ ከፍተኛ አመኔታ የነበራቸው እና ወታደራዊ ችሎታቸውም የላቀ እንደነበረ እና እነዚህ ልዩ ተዋጊ የኮማንዶ ሃይሎች ‘በሌ/ል ኮለኔል ጀማል

መሐመድ ሳልሕ’ የቅርብ ተንከባካቢነት ለ 4 ወራት የሰለጡ ልዩ ኮማንዶ ሃይል ነበሩ።

ይህ ድርጅት በተለያየ ጊዜ እና በልዩ ልዩ አሰልጣኞች የሰለጠኑ ልዩ ኮማንዶዎች ቢኖሩትም ፤ እነኚህ 400 ኮማንዶዎች ግን ልዩ ወታደራዊ የማጥቃት ስልጠና የወሰዱና ልዩ ተልዕኮ አንዲፈጽሙ የላቀ ትኩረት የተደረጋለቸው ተዋጊዎች እንደነበሩ ታዉቋል። አስገራሚው ነገር፤ እነኚህ ኮማንዶዎች “ዊዓ” ውስጥ ልዩ የኮማንዶ ስልጣና ወስደው ምረቃቸውን እንዳጠናቀቁ ነበር የወጡት።

በሚያስደንቅና በሚገርም ቅጽበታዊ ሁኔታ እንዴት እና በምን ታምር እጅግ የተጠናከረ ነው በሚባልለት መከላከያ ድምበር ጥሰው ሊወጡ ቻሉ? ምሽግ ውስጥ የነበረው የኤርትራ መከላከያ ሃይልስ እንዴት ሊጥሱት ቻሉ? እንዲህ ዓይነት ብዛት ያለው ሃይል ለማስወጣት ዝግጅት ሲደረግ ለምን እና እንዴት ሲሆን ነው አስቀድሞ ይህ የዝግጅት ምስጢር ሊነቃበት ያልተቻለ?

ከአስመራ፤ዓላ፤ባፅዕ (ምፅዋ)፤ከርን እና ከተለያዩ ግምባሮች እንዲህ ዓይነት ብዛት ያለው ሰራዊት አሰባስቦ ወደ አንድ

የመገናኛ ቀለበት ባጭር ጊዜ ሲሰባሰብ፤ እንዴት ሊነቃበት አልቻለም? ለምንስ ያቺኛዋ ዐ/ዜሮ ሰዓት ተመረጠች? ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ ይሻሉ?

በቁጥርና በስፋት በየምሽጉ የሚገኘው የኤርትራ መከላከያ ሃይል መንግሥት እንደሚለው የቁጥር ብዛትና የመጠሪያ ስማቸው ሳይሆን፡ መሬት ላይ ያለው እውነታ ግን የሰው ሃይል ብዛቱ የተመናመነ መሆኑን ውሎ ያደረ ሃቅ ነው። ለዚህም አስተዋጽኦ ያደረገው፤ በግድ እየተመለመለ ወደ ወታደራዊ ስልጠና እንዲሄድ የተገደደው 'አገራዊ አገልግሎት' በሚል ስም የሚጠራው ያልተገደበ ወታደራዊ ባርነት ምክንያት ምሽጉን እየጣለ ወደ ከተማ የሚኀርፈው እና አገሩ ትቶ ድምበር ጥሶ ወደ ስደት የሚኀርፈው ወጣት ምክንያት ምሽጉ ክፍት ሆኖ የሚጠብቀው ወታደር እንደሌለ የሚታወቅ ነው።

ቢሆንም፤ ብዛት ያለው እንዲህ ያለው ተዋጊ ሃይል፤ ድምበር ጥሶ ሊወጣ የቻለው፤ ከላይ የተጠቀሰው ምክንያት አስተዋጽኦ ቢኖሮውም፤ በተመናመነ ቁጥር ምሽግ ላይ የነበረው የተቀረው ድምበር ጠባቂ ሠራዊትም ቢኖርም ፤ ሃላፊነቱን ለእርሱ ብቻ ማሸከም አግባብነት የለውም።

ይህ ጉዳይ በሚመለከት፤ በጥልቅ መመርመር ያለበት ምስጢር 'ከምሽግ በፊት እና ከምሽግ በኋላ" በአገራዊ

ደህንነት ወኪል **“በኮለኔል ዮናስ ፍጽአምላክ”** ስር የሚገኙት ‘ልዩ አገራዊ የድምብር ደህንነትና የፀጥታ ክትትል ጉዳይ የስለላ ክፍሎች’ አስተዋጽኦ ምን ነበር? የሚል ጥያቄ ለኔም ሆነ እንደ እኔ ለመሳሰሉ ብዙ ኤርትራዊ ዜጋ አነጋጋሪ ጉዳይ ሆኖ አግኝተነዋል።

የድምህቱ መሪ ሞላ አስገዶም፤ ለአንድ አመት ያክል ከወያኔ መሪዎች ጋር ምስጢራዊ ግንኙነት በማድረግ በመረጠው ጊዜ እና ቦታ በማቀድ ይህ በድል የተቀናጀበት ኦፐሬሽን ለማጠናቀቅ ደምብሩን ጥሶ ሲያልፍ በሂደት አንዳንድ እክሎች ቢገጥሙትም፤ ያለ ምንም ችግር ድምበሩን በጥሶ ከሰራዊቱ ጋር እንዳተሻገረው በይፋ ገልጿል።

**“ኦፐሬሽን እንቁጣጣሽ”** ብለው ኢትዮጵያዊያን የሚጠሩት ትኩረት የሳበ ይህ አስገራሚ ወታደራዊ ክንዋኔ ሲካሄድ፤ በሁለቱም ወገን አነስተኛ የሆነ የሞት እና የመቁሰል አደጋ እንዳጋጣመ አልሸሸጉም። በሞላ አስገዶም በኩል የሚመራው ተዋጊ ሠራዊት ድምበር ለመጣስ በተደረገው ውግያ፤ የደረሰበት ጉዳት መጠኑ ባይገለጽም፤ በእኛ በኤርትራ በኩል ግን የደረሰው ጉዳት **27 ወታደሮች ሲሞቱ፤** በርካታ ወታደሮች ደግሞ የመቁሰል አደጋ አንዳጋጠማቸው፤ በዚህም የተነሳ፤ **የተሰነይ ሆስፒታል** ተጣብቦ አንደነበረ፤ ከኤርትራ የስለላ አባሎች የተገኘ ምስጢራዊ ዘገባ ያስረዳል።

በዚህ ወታደራዊ ክንዋኔ ስንመለከት በእኔ እና በመሰል ኤርትራዊያን እየተነሳ ያለው ጥያቄ፤ የኢትዮጵያ የስለላ ክፍሎችና ባለስልጣኖች የዘረጉት ምስጢራዊ የስለላ ሰንሰለት፤ ከሞላ አስገዶም ጋር ብቻ የተወሰነ ነበር? ወይስ ከዚያ ባሻገር ርቆ እስከ የኤርትራ ባለሥልጣኖች ድረስ የተዘረጋ የስለላ መረብ ነበር? የሚሉ ጥያቄዎች ጭሮውብናል።

ይህ በኤርትራዊያን ዜጎች እየተነሳ ያለው ጥያቄ ማንሳት አግባብነት ያለው ነው። የኢትዮጵያ የፀጥታ ክፍሎች ውስጣችን ድረስ ሰርጸው በመግባት እንዲህ ያለ ወታደራዊ ክንዋኔ ለማካሄድ የቻሉበት ምክንያት ግምት ውስጥ የምናስገባቸው ጉዳዮች አሉ። እነሱም፤ እንዲህ ያለ ክንዋኔ ለማካሄድ ፤በውስጣችን ሊገቡ የቻሉት ‘አምነውበት ወይንም በቅጥረኛነት፤ የተመለመሉ በመንግስት ውስጥ ያሉ የስለላ ሃላፊዎች ንኪኪው ሳይነካቸው አልቀረም።

እንዲህ ያለ ጥርጣሬ ሊያሳድርብን የቻለውም በእርግጠኛነት የተጨበጡ መረጃዎች ሾልከው እየወጡ ናቸው። ሞላ አስገዶም እና የቅርብ ታማኝ አባል ሰራዊቶቹ የመንግስታችን ወታደራዊ መኮንኖች እና ባለስጣኖች የግል ባሕሪዎቻቸው እየተከታተሉ ምን እንደሚመስሉ ለአመታት በሚገባ አጥንተዋቸዋል። እነኚህ በገንዘብና በጥቅም ስግብግብነት የተጠመደ ባሕሪ ያላቸው ኤርትራዊያን ባለሥልጣኖች ምንነት

በቃላሉ ተጠቅመው ለወያኔ ባለስልጣኖች የስለላ ክፍሎች በማስረዳት ደካማ ጎን አግኝነተው ስለላው በቀላሉ በስፋት በመዘርጋት ሊያከውኑት ችለዋል። መታወቅ ያለበት ጉዳይ በርካታ የመንግሥት ባለሥልጣኖች የማአረግ እና የደሞዝ ጭማሪ ጥያቄ ባግባቡ መልስ ሊያገኙ ስላልቻሉ፤ በእረስበርስ ቂም እና ሽኩቻ ውስጥ እንዳሉ ሁላችን የምናውቀው ሃቅ ነው።ስለሆነም አገራዊ የሕሊና ትኩረታቸው የተንሻፈፈ አድርጎታል።

ዛሬ በጣት የሚቆጠሩ ባለሥልጣኖች በስተቀር፤ የመንግሥት ሠራተኛ እና ተራው ሕዝብ በዚህ ስርዓት እፎይ ብሎ የተኛ ዜጋ የለም።አገራችን በየትኛውም እቅጣጫ ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁልቁል እየሄደች እንዳለች፤ ኢሳያስ ወደ ገደል ይዟት እያመራ እንዳለ፤ ሕዝብ እየተበታተነ መሆኑን፤የወጭ እና የውስጥ ተቃውሞ በዚህ ሥርዓት ላይ እየጨመረ መሄዱን፤ የዓለም መንግሥታት ትኩረታቸው እየጠነከረ መሄዱ ተደማምሮ የሕዝብ ተስፋና ባለሥልጣኖች እየጨለመ መሄዱ፤ አገር ውስጥ የምንኖር ዜጎች የምናውቀው ጉዳይ ነው።

ይህ የጨለመ ስዕልም ወያኔ በሚገባ ተረድታዋለች;።በተለይም ደግሞ በሰለላ መረብዋ በሞላ ስገዶም በኩል የሸረሸረቺው መሬት ላይ የታየው ሁኔታ በሚገባ እንደተጠቀመችበት የሚያጠያይቅ አይደለም።

የራሳቸውን መንግሥት (ሻዕቢያን) ውስጥ ለውስጥ እና በገሃድ የሚያሙትና መጪው ዕደላቸው የጨለመባቸው፤ በተለያዩ መንግሥታዊ እርከን የሚገኙ የመንግሥት ሐላፊዎች፤ በኢትዮጵያ የስለላ ሃይሎች አቅጣጫቸው/አስተሳሰባቸው እንዲስቱ አንዳላስቸገራቸው ያየነው ገሃድ መረጃ ነው። እንኳን እና ከላይ የተጠቀሱት ክፍሎች ይቅር፤ የወያኔ የስለላ ሰንሰለትን ለማምከን የተመደቡ ከመንግስት ጋር ግጭት የሌላቸው በምቾት የሚኖሩ ባለሥልጣኖች ሳይቀሩ በግል ጥቅም በስግብግብነት ባሕሪ ተጠምደው ጥቅማቸው ለማሳደድ ሃላፊነታቸው አዝረክርከው ወዲያ ወዲህ ስለሚሯሯጡ፤ በላያቸው ላይ ሲፈጸም የነበረው ስለላ እና ደባ ምንም እውቀት እንዳልነበራቸውና ምስጢሩን ሊደርሱበትና ሊከላከሉት እንዳልቻሉ አመላካች ክስተት ነው።

እንዲህ ያለ የስለላ ድክመት በተለያዩ ጊዜያት ያየናቸው የታዩ ሃቆች አሉ። በርካታ ባለሥልጣኖች ኢሕጋዊ በሆነ ጥቅም ተዘፍቀው ልጆቻቸው እና በልጅ ልጆቻቸው ዕድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ወጣቶች በገንዘብ እየተደለሉ በሕጋዊና በምስጢር ወደ ውጭ አገር አንዲሻገሩ ያደርጋሉ።በዚህ ባሕሪ ተጠምደው የተመደቡበት ሙአቸውን ዘነግተው “በእንካ አምጣ” ግብይት ውስጥ ተጠምደው ይገኛሉ።ይህንን ግብይት ለማስኬድ ፤በአየር፤በመሬት፤በባሕር እና በመሳሰሉ

መንግሥታዊ ሰንሰለቶች ተጠቅመው፤ ያለምንም ሓፍረት ዜጎች በሽግግር ገባያ ወደ ውጭ እንዲሄዱ ያደርጋሉ።

በነዚህ የተጨማለቁ ባለሥልጣኖች አሰራር ምክንያት የተበሳጨ አገሩን እየጣለ ከሚጎርፈው ወጣትና አዛውንቶች ከ80 ሺሕ እስከ 400 ሺሕ ናቅፋ እየተቀበሉ፤ የመንግስት መኪኖች፤ የመታወቂያ ሰሌዳዎቻቸው እየቀያየሩ፤ ከኢምግሪሺን እና ከፕረዚዳንቱ ጽ/ቤት ሐላፊዎች ጋር እየተመሳጠሩ፤ በዚህ የሰው ማሸጋጋር ግብይት ውስጥ የገቡ ብዙ ጉሬዛዎች አሉ።

ይህ አልበቃ በሎአቸው፤ በተጨማሪ አገራዊ አግልግሎት ውስጥ በሚገኘው ወጣት በግል እርሻዎቻቸው እና የቤት ግንባታ ውስጥ አሰማርተው ነፃ ጉልበት በመመዝመዝ ላይ ይገኛሉ።ገንዘብ ከፍሎ ወደ ውጭ አገር መውጣት ያልቻለ ወጣት የድሃ ልጅ ደግሞ ከባርነት ባልተናነሰ ነፃ ወታደራዊ አግልግሎት ተረግጦ መያዙን አላንስ ብሎ፤ ወታደራዊ ቅጣት በመቅጣት ሕሊናውን ሲያደክሙት፤ ይህ ግፍ መሸከም አላስችል ሲለው፤ ተበሳጭቶ ደምብር ጥሶ በመሰደድ የሲናይ ምድረበዳ ሽፍቶች እና የባሕር ዓሳ ነባሪ ሲሳይ ሆኖ እንዲቀር እያደረጉት ነው።

እነኚህ በመካከለኛ እና በከፍተኛ የሥልጣን እርከን ውስጥ የሚገኙ ባለስልጣኖች፤ ይህ የገንዘብ ክምችት ስግብግብነት

አልበቃ ሲላቸው ከኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች መሪዎች ገንዘብ እየተቀበሉ ብዙ ንብርት እንዳከማቹ የነዚህ ቤተሰብ የሆነ የቅርብ ጓደኛዬ ከማገኘው ምስጢር ለማረጋገጥ ችያለሁ።

እነኚህ ከፍተኛ የኤርትራ ባለሥልጣኖች በሹመትና በጥቅም እርስ በርስ ስለሚነታረኩ፤ ቂም ውስጥ ገብተው፤ ከኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሓይሎች ጋር ሆነው ምስጢራቸውን ለውጭ ሃይል ሳይደብቁ እርስ በርስ ስም እየጠቀሱ አንዱ አንዱን እንደሚያማ እና ምስጢሮችንም እንደሚያዝረከርኩ ተስተውሏል።

ለምሳሌ በዚህ ጉዳይ እንደማስረጃ የሚጠቀሰው፤ ለረዢም ጊዜ የድምበር ጉዳይ ክትትል ሐላፊ፤ የኢትዮጵያ እና ሱዳን ተቃዋሚ ሃይሎች አስተባባሪ፤ከዚያም የሕዝባዊ ሠራዊትና፤ መደበኛ የመከላከያ ሃይል ክምችትና ስምሪት ሆኖ ያገለገለ፤ አሁን ደግሞ በቀርቡ የምዕራብ ዕዝ ድምበር ሠራዊት የበላይ ተቆጣጣሪ ሆኖ የተመደበው፤ ብርጋዴር ጀኔራል ተኽለ ማንጁስ፤ ከኤርትራ የመከላከያ ሃይሎች ስታፍ ዋና አዛዥ ከሆነው ከጀኔራል ፍሊጶስ ጋር የቆየ ጸብና አለመግባባት፤ ያለውን ምስጢር ዘክዝኮ ለኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃላፊዎች እንደነገራቸው ሰምቻለሁ። ጀኔራል ፍሊጶስም፤ “ሳይመን” ለሚባል ልጁ “ይህ ዕውር (ተክለ ማንጁስን ነው ዕውር

እያለው ያለው)፤ ቀን እና ሌሊት ለእሱ ባደሩ ውሾቹ በኩል እየሰለለን ስለሆነ የዛው ግዳጅ ተጠቂ እንዳትሆን አደራ፤ ብሎ አንዳስጠነቀቀው “ሳይሞን” በአልኮላዊ መጠጥ ሃይል ተሸንፎ በነበረበት ወቅት “ተኽለ ማንጁስ” በጆሮው አንደሰማው ተናግሯል።

ዛሬ ከፍተኛ የኤርትራ ባለሥልጣኖች በኢሳየስ ላይ መተማመናቸው ተስፋ የመነመነ መሆኑን ሕዝብ ያውቃል። እነሱም ቢሆን በኢሳያስ ምክንያት ለሥልጣናቸው ሲሉ፤ ቁጥር ስፍር በሌለው በንቅዘት ገበን ውስጥ ገብተው በመጨማለቃቸው፤ከተጠያቂነታቸው እንደማይድኑ ስለሚያውቁ፤ አዘቅት ውስጥ ገብተው መውጫ ቀዳዳ አጥተው ጭንቅ ውስጥ እንዳሉ ይታወቃል። ስለዚህም እንደ አማራጭ የሚወስዱት፤ “የአባት አገር ሲወረር፤ አብረህ ውረር” እንደሚባለው፤ በዚህ በዘመነ ሰርቆትና ስርዓተ አልባነት፤እራስክን “አታስርብ” በሚል የግል መመሪያ፤ እንደምንም ብለን ለልጅ ልጆቻችን የሚተርፍ ንብርት ማካበት አለብን ብለው በዛው ንቅዘት እየተዳዙ ይታያሉ።

ይህ የባለሥልጣኖቹ የንቅዘት ባሕሪ መዘፈቅ ስንመለከት፤ በሞላ አስገዶም በኩል ብቻ የተከናወነ የስለላ ክንዋኔ የተወሰነ ሳይሆን እንዲህ ያለ በቁጥር እጅግ ከፍተኛ ተዋጊ ሃይል ድምብርን በቀላላ ጥሶ ለማለፍ የነዚህ በንቅዘት የተዘፈቁ

ባለሥልጣኖች እጅ እንዳለበት የሚያጠራጥር አይሆንም። ሞላ አስገዶም ለአንድ አመት ያክል ከወያኔ የስለላ ክፍሎች እየተገናኘ ፤ እንዲህ ያለ ሰፊ ሰራዊት፤ በአንድ የተቀራረቡ አቅጣጫዎች ከመቅጽበት "ሆ ብሎ!" አስሰልፎ፤ ወደ ኢትዮጵያ ለማሻገር ሲያደራጅ መቆየቱ፤ ይህ ሲያደርግ "ያለ ምንም ፍርሃት እና ስጋት ለዚያ ያህል ጊዜ መቆየቱ" ፤ዓይን እና ጆሮው ከፍተኛ ነው እየተባለ በስለላ አወቃቀሩ የታወቀው ነው የተባለለት የኤርትራ መንግሥት፤ ስለ ሁኔታው እውቀት አልነበረውም ለማት ያስቸግራል። ዕደሜ ከሰጠን አሁንም ገና ለወደፊቱ ሌላ ፍጻሜ ማየታችን አይቀሬ ነው።

የአገራችን የስለላ ግንብ በወያኔ መቀደዱና በቁሙ የበሰበሰ የስለላ ግምብ መሆኑ ዓይናችን እያየን ነው። ይህ ደግሞ ካሁን በፊት ተደጋጋሞ ታይቷል። ለምሳሌ ሁላችን እንደምናስተውሰው ጥር 21/ 2013 የመንግሥት ግልበጣ ለማከናወን በሚል የሆነውን ክስተት ስናስታውስ **"ወዲ ዓሊ"** እና፤ **"ሳልሕ ዑስማን"** ከዓዲ ኳላ እና ከፆሮና አካባቢ ወደ 100 ኪ.ሜትር የሚያክል ርቀት፤ ታንኮችና ሜካናያዝ መኪኖችን ይዘው፤ በርካታ ከተሞችና ገጠሮች ተጉዘው፤ በመሃል የአስመራ ከተማ ሰንጥቀው፤ ወደ ፎርቶ ገብተው "የአገሪቱ መአከላዊ የዜና ጣቢያ ማሰራጫ" እስኪቆጣጠሩ ድረስ፤ የኢሳያስ የስለላ መዋቅሮች ምንም እውቀት እና መረጃ አልነበራቸውም።

ኢሳያስ በለመደው የውሸት ባሕሪው **“እናውቅ ነበር፤ ዝም ብለን እንዲያልፉ ያደረግነው ትያትራቸውን እንድናስጨርሳቸው ብለን ነው፤ ያ ፊልም እንከታተለው ነበር.....ወዘተ .......ወዘተ...”** ሲል በስለላ ያዋቀራቸው ሰላዮቹ ሐፍረት ለመሸፋፈን እንዲህ ያለ የውሸት ንግግር በሚዲያ ቢናገርም ፤ ኢሳየስ የተናገራቸው እነኚህ አስቂኝ ንግግሮች፤ የለመድናቸው የኢሳያስ “ተረት-ተረት ንግግሮች ናቸው”። ሓፍረታቸውን ለመሸፍን ደግሞ ማለት የሚችሉት ያ ብቻ ነው።

ሞላ አስገዶም ሳናውቀው አመለጠን፤ ለጥቂት አመለጠን የሚሉ ካሉም “የዋሃን መሆን አለባቸው”። ከላይ የተጠቀሰው የመንግሥት ግልበጣ የተባለው በወዲ ዐሊ የተመራው ክንዋኔ፤ ኢሳያስ አስቀድሜ አውቅ ነበር ቢልም፤ ዓለም በሞላ ያዳረሰ ኢሳያስን ያጋለጠ ጣቢያው በተቃዋሚ ወታደራ መኮንኖች በቁጥጥር ስር የመዋሉን ጉዳይ “ወደ ጎን እንተወው እና”፤ ኢሳያስ ይህን ምስጢር አስቀድሞ ያወቀው ቢሆን ኖሮ፤ በዜናው ክፍል ውስጥ ሠራተኛ የሆነቺው የገዛ ልጁ “ኤልሳ ኢሳያስ” በጣቢያው ውስጥ እንዳትገኝ አስቀድሞ ትዕዛዝ ያስተላልፍ ነበር። ሀኖም እርስዋም እዛው ተገኝታ “ታግታ/ሆስተጅ’ ሆና ከተቀሩት ጋር አብራ ተይዛ በዋለቺው ልጁ በኤልሳ ፍጹም አይጨክንም ነበር።

የፎርቶ ክንዋኔ አንዳንድ የስላላ ክፎሎች ምስጢሩን አያውቁትም ነበር ማለት ግን አይደለም።ምናልባት **‘ለውጥ ይመጣ ይሆን’** በሚል ተስፋ ምስጢሩ በምስጢር ይዘውት እርምጃ ከመውሰድ የተቈጠቡ የስለላ ክፍል አባሎች አንዳሉ እኔ በግል የማውቃቸው አሉ።ዝምታቸው ለለውጥ ካላቸው ምኞት የተነሳ ነው። ሆኖም የእንቅስቃሴው ሙከራ በራሱ ምክንያት ሳይሳካ ቀርቶ የኢሳያስ መፎከሪያ ሆኖ ቀረ።

አሁንም በተመሳሳይ ሞላ በሙቶዎቹ የሚቆጠሩ ወታደሮቹ ይዞ ድምበራችን ጥሶ ሲያልፍ፤ ሌላ ቀርቶ ሌ/ኮሎኔል ይሳቅ ፤ ሌኒን (ኮ/ል ፍፁም) ምስጢሩን አንደሚያውቀው እርግጥ ነው። ሌኒን ከሞላ አስገዶም ሌላ ምስጢሩን የሚያካፍለው ሰው አንዳልነበረው በሌኒን ዙርያ ያሉ እስታፍ አባሎች የሚያውቁት ጉዳይ ነው።

ዲምህት ይህን ያህል ወታደሮች **ከአስመራ ከተማ** የድምህት ጽ/ቤት፤ **ከምጽዋ፤ ከዓዲ-ኳላ፤ከከረን፤ ከሓረና፤ ከዓሻ ጋላ** እና ከ**ዓላ** የድርጅቱ የኪነት ባሕል ቡድን፤ ወደ አንድ መሰባሰቢያ ቀለበት ወደ ‘እምነ ሐጀር’ በአንዳች ቅጽብት ሊሰባሰብ ቀርቶ፤ ሌኒን ሳይፈቅድ አንድ የድምህት ጋንታ/ሃይል በዓይን ርቀት ወደ እሚታይ ጉዞ  እንኳ “አንድ ኢንች “መንቀሳቀስ የማይችሉ እንደነበረ የምናውቀው ሃቅ ነው። እነ ኮለኔል ፍጽ-አምላክም ሆነ ተኽለ ማንጁስ ቢያንስ ለ10 አመታት ይህን

የተቃዋሚ ሃይል በቀርብ ይቆጣጠሩትና እና ይመሩት ስለነበሩ፤ሁኔታው ስለማያውቁት አልነበረም።

ምናልባት አላወቁም የሚባሉ ከሆነም፤ እነ **“ንጉሠ ዱማ”** እና **ሃይል 65** የተባለው ክፍለሰራዊት አባሎች ብቻ መሆን አለባቸው። በቀላሉ ክስተቱ ስኬታማ ለመሆን ባሁኑ ሁኔታ እየታየ ያለው፤ ባለስልጣኖች መሃል እየታየ ያለው ያለመስማማት ውጤት ነው።

ለምሳሌ ፕረዚዳንት ኢሳያስ በወዲ ካሳ የሥራ አፈጻጸም ጉድለት ምክንያት ባለመደሰቱ የተፈጠረው ያለመጣጣም የቆየ ቢሆንም፤ ቅራኔው እያየለ ሄዷል። ኢሳያስ ለወዲ ካሳ **“ወደ ጠላት ጉያ ሰርጋችሁ ለመግባት እንድትችሉ በሚል ልዩ በጀት ተመድቦላችሁ እያለ፤ በወያኔ ሰላዮች ላይ አስፈላጊው እርምጃ መውሰድ አልቻላችሁም”** በማለት ሲያስፈራራው ቆይቷል። አሁን ደግሞ ይህ ብዛት ያለው የደምህት ታጣቂ ሠራዊት ድምበር በጥሶ ወደ ኢትዮጵያ መሻገር በተያያዘ ጉዳይ ኢሳያስ በወዲ ካሳ ለይ ቁጣው አጠንክሮበት እንዳለ እኔ በምሰራበት ክፍል ውስጥ ሳይቀር ነፀብራቅ/ምልክት እየታየ ነው።

ከዚህም ተያይዞ በፍሊጶስ እና በተኽለ ማንጁስ መሃል በሞላ አስገዶም መሪነት የታየው ወታደራዊ የስለላ ክንዋኔና በቅዱስ ዮሓንስ ዋዜማ ደምበር ጥሶ መሄድ የተነሳ፤ በሁለቱም መሃል የቆየው አለመግባባት፤ ወደ ከፍተኛ ውጥረት ተሻግሯል።

ተኸለ ማንጁስ የቅዱስ ዮሐንስ አውደአመት ከቤሰቡ ጋር ለማክበር ሲል ወደ አስመራ ሄዶ ስለነበር፤ ከወዲ ፍሊጶስ ጋር ወደ ምድብ ቦታህ **ተመለስ አልመለስም** የከረረ ንትርክ አንስተው እንደነበር ሰምተናል።

የድምህት ወታደራዊ ክንዋኔ የተካሄደበት ዕለት ምዕራባዊ ግምባር የሚባለው 'ሓሬና፤ጉልጅ፤ ተሰነይና የመሳሰሉ ወታደራዊ የምሽግና የስለላ ከፍተኛ ሃላፊዎች፤አብዛኞዎቹ ለቅዱስ ዮሐንስ በዓል ለማክበር ወደ አስመራ ተጉዘው በነበረበት ወቅት ነበር የተከናወነው። ታዲያ እቦታው ላይ ባለመገኘታቸው የተገኘ ክፍተት ተጠቅሞ ይሆን የሞላ አስገዶም ክንዋኔ ሊሳካ የቻለው? የሚል ጥርጣሪ ሊነሳ ይችል ይሆናል። ሆኖም መጠርጠሩ ተገቢ ቢሆንም፤ ይህ ምክንያት በደረቁ እንዳለ ለሁኔታው መሳካት በቂ ሊሆን አይችልም።

በዚህ ነጥብ ላይ ነጥሎ ብቻውን ማስቀረት የማይቻል ነጥብ፤ ቢኖር ፤ ለቅዱስ ዮሓንስ በአል ለማክብር ብለው ክፍት ትተውት የሄዱት የስላላ ባለስልጣኖች **"ክንዋኔው ሲደረግ፤ እቦታው አልነበርንም"** ብለው እንደ የማምለጫ ሽፋን ለመጠቀም እንዲያስችላቸውና፤ ክንዋኔው ሲፈጸም መረጃ እንደሌላቸውና ምንም የሚያዉቁት ነገር እንደሌለ ተብሎ እንዲታለፍ፤ በጥናት ከወያኔ የስለላ መረቦች ጥበባዊ የሽፋን ዘዴ የመነጬ ስምምነት ይሆን የሚለውንም አብሮ መታሰብ

አለበት። ምክንያቱም፤ የተከናወነበት ወቅት/በአውዳመት ዕለት መመረጡ በጣም አስገራሚ ንድፍ በመሆኑ።

ሞላ አስገዶም በይፋ እንዲገልጸው ያልፈለገው ምስጢራዊ ክንዋኔው አምቆ ለሕዝብ አይነገርም ተብሎ ይዞት ካልሆነ በስተቀር፤ ሁኔታዊ ከተጠቀሱት የአካባቢው የስለላ ሃላፊዎች ጋር ግንኙነት አድርጎ አንደነበር ያፈነገጡ ወሬዎችም አሉ። በዛሬይቱ ኤርትራ ባለሥልጣኖች የሚያደረጓቸው ክንዋኔዎች በድብቅ የሚያዝ ለሕዝብ የማይደርሱ ምስጢሮች የሉም።

ዛሬ ምስጢር የሚባል በባለ ስልጠኖች ዘንድ አይታወቅም። ለምሳሌ ብርጋዴር ተኽለ ማንጁስ ከፕረዚዳንት ኢሳያስ ጋር የነበረው ጥብቅ ግንኙነት ተሰሚነቱ ተነጥቆ ወደ ምዕራባዊ ቆላ የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች የበላይ ተቆጣጣሪ ሆኖ ሲላክ፤ ከባድ ፤ከባድ የሆኑ ብሔራዊ ምስጢሮች ላንዳንድ ተቃዋሚ መሪዎች ያካፍላቸው አንደነበረ ታውቋል።

ለምሳሌ፤ ፕረዚዳንት ኢሳያስ ለፍልስጢኤም ተዋጊ ሃይሎች ወታደራዊ መሳሪያ ለመላክ እንዲያመች **ሲ አይ ኤ** ሳያወቅ እንዴት መላክ አንደሚቻል፤ 4 ጀኔራሎች አስጠርቶ ካወያያቸው በኋላ፤ ወዲ ካሳ እና ተኽለ ማንጁስ ‘ሲ አይ ኤ’ ሳይደርስበት መሳሪያዎችን ማሽጋጋር የሚቻልበት **ዘዴ** ስላቀረቡ፤ የሁለቱም ጀኔራሎች ሃሳብ አጥጋቢ ሆኖ ስላገኘው፤ ኢሳያስ በጣም መደሰቱን፤ ይህ ምስጢር ላንዳንድ የኢትዮጵያ

ተቃዋሚ መሪዎች አጫውቶአቸው እንደነበርና ተቃዋሚዎቹ እራሳቸው ከኮሎኔል ፍጹም ሰራተኞች ጋር መጠጥ ቤት ተገናኝተው እንዳወርዋቸው ሰምተናል።

እስከዚህ ድረስ ብሔራዊ የሆኑ አገራዊ ከባድ ምስጢሮች ለባዕድ ተዋጊ ሃይሎች የሚዘከዝኩ ጀኔራሎች መኖራቸው፤ ባጠቃላይ ስንገምግም፤ ውስጥ ለውስጥ ሲሸረብና ሲዘረጋ የነበረ የወያኔ የስለላ መረብ ለማወቅ ችሎታው የተዳከመ እንደሚሆን አያጠራጥርም ።

ማዓዛው ጌጡ ከሚባል ለአመራራ ብቃት የማይመጥን በአባሎቹ እምብዛም የማይወደድ የአርበኞች ግምባር መሪ ፤ ኮሎኔል ፍጹምን በገንዘብ ጥቅም ስለያዘው መሪነቱ ለብዙ ጊዜ ይዞት እንዲቆይ ኮሎኔል ፍጹም እንደ የበላይ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች ተቆጣጣሪና አዋሃጅነቱ መዓዛ ጌጡ ሥልጣኑን ይዞት እንዲቀጥል አድርጓል። **አሚነ ነጋሽ**፤ **ዓወት ፍስሓ** የመሳሰሉ ኤርትራዊያን ነጋዴዎች ጋር እየተገናኘ ከዲአስፖራም ሆነ ከተለያዩ ምንጮች ለድርጅቱ የሚመጣለትን ገንዘብ እንዲነግዱበት ለመአዛ ጌጡ በኩል እያዘዘ ስለሚያካሂደው የንግድ ክንዋኔ በገሃድ ይታወቃል። ወደ 10 የሚሆኑ ታዋቂ ነጋዴዎች ከመአዛው ጌጡ እየተበደሩ፤ ብድሩን ሳይመልሱት እንዲቀሩ የተደረገበት ምክንያትም፤ ኮ/ል

ፍጹም ከነጋዴዎቹ ጋር ወግኖ ማአዛው ጌጡ ያበደራቸው አረጣ እንዳይጠይቃቸው ተጽእኖ ስለሚያደርግለት ነው።ይህ

ማንም የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅት መሪም ሆነ አባል ኤርትራዊት ሴት ጋር የጾታ ግንኙነት በወድም ሆነ በግድ በምንም መልኩ እንዳያደርግ በጥብቅ የተከለከለ መሆኑን ከራሱ ከኢሳያስ ሰርኩላር/ዘዋሪ ትዕዛዝ የተላለፈ ቢሆንም ኮለኔል ፍጹም ከማአዛ በሚያገኘው በሺዎች የሚቆጠር የዶላር ጥቅም ግንኙኙነት ምክንያት በመታወሩ፤ **ሰላም ሃይለ** ከምትባል ኤርትራዊት ጋር ትዳር መስርቶ ሁለት ልጆች ወልዶላት ምንም አልሆነም። ጋብቻው እንዲፈጸም የሰርጉ/የጋብቻው ዋና አባት ሆኖ ያዘጋጀው ደግሞ እራሱ ኮሎኔል ፍጹም ነው።

ሌኒን/ኮሎኔል ፍጹም በጥቅም ስግብግብነት በመታወሩ ለተቃዋሚዎች የሚታደል በሚል ስም 'ክላሽን፤ብዙ ሺህ የሚቆጠር የመሳሪያ ጥይቶች፤ ኤም 14፤ እና መትረየስ መሳሪያዎች' ለራሻይዳ ወሮበላዎች፤ በጥቁር ገበያ እየሸጠ ሰዎች የሚጠለፉበት መሳሪያ የሚያቀርብላቸው ሌኒን ነው። ይህ ደግሞ በእነ ካፒቴን ዳዊት ዘርዓይ አማካኝነት ገበያው ይከናወናል። በእንዲህ ዓይነት ዝቅጠት የተበላሹ የኤርትራ የስለላና የወታደራዊ ሃይል አዛዦች ኤርትራ ምድር ውስጥ እየተካሄደ የነበረው የኢትዮጵያ የስለላ መረብ ሊደርሱበት

አይችሉም ብቻ ሳይሆን፤ በጥቅም በመበላሸታቸው የስለለው ካፋዮች ከመሆን የሚያግዳቸው የሞራል ገደብ የላቸውም።

‘**ሃይለ ሞባይል**’ የሚባል ኤርትራዊ በኮ/ል ፍጹም አሰማሪነት በሱዳን በኩል አድርጎ ወደ ኢትዮጵያ እየገባ፤ ወደ ሱዳን /ሓምዳይት ሸቀጣ ሸቀጥ እንዲያስገባ ካደረገ በኋላ፤ **ሰመረ ርዕሶም** የተባለው ደግሞ ከሃይለ ሞባይል ተቀብሎ ከሓምዳይት ወደ ኦሞ ሓጀር በኩል በ7 የጭነት መኪኖች እያጓጓዙ ያለ ምንም የጉምርክ ቀረጥ እንዲገባ ትዕዛዝ በመስጠት እርሱ እና መሰሎቹ በእንደዚህ ዓይነት የንቅዘት ባሕር የዋኙ ስለሆኑ ፤ ወያኔ ለእንደዚህ ዓይነት የነቀዙ መኮንንኖች እና የስላላ መዋቅሮች በቀላሉ በጥቅም እንደሚጠልፋቸው፤ “የስለላ እና የንቅዘት ግንኙነት ባሕሪ” የማያውቅ ብቻ መሆን አለበት።

እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያ የስለላ መረብ በኤርትራ መንግሥት ላይ የፈጸመው ምስጢራዊ የስለላ ጦርነት፤ ብዙ ቢሆንም፤ አንዳንዶቹን ወደ ሗላ ዞር ብልን እንምልከት።

ባለፈው ጊዜ ማለትም በምርጫ 5/2000 (አውሮጳ አቆጣጠር) በመጨረሻው ጦርነት ወቅት፤ ወያኔዎች ባልታሰበ ጊዜ በፈለጉት ቦታ እና ሰዓት ድንገተኛ ወታደራዊ ጥቃት በዛላምበሳ በኩል በፈጸመበት ወቅት፤ መላው ኤርትራ ተናውጦ ነበር። ይህ ደግሞ የሚያሳየው፤ የስለላ ጥበባቸው ምን ያህል እንደሆነ ነው። በዛ ውርደት የደረሰብን ጥቃት የተነሳ፤ ባረንቱ ላይ ሠራዊትና ዋና ዋና የክፍል አዛዦች

ሰብስበው፤ ፍሊጶስ የተናገረው ስናስታውስ “**ወያኔዎች በስለላ ጥበብ መጥቀው በመሄዳቸው በልጠውናል፤ የስለላ ክፍላችን ምን እየሰራ እንደሆነ ግምገማ መደረግ አለበት**” ሲል እንደተናገራቸው እናስታውሳለን።

ለስርዓቱ በጣም ቅርብ የሆንን ጥቂት ሰዎች እንደምናውቀው፤ በተለያዩ ቦታዎች ድንገተኛ ጥቃት እየተፈጸመ በተከታታይ ሲከናወን፤ የስለላ ክፍሎቻችን ከገመቱት በላይና ከቁጥጥራቸው በላይ በመሆኑ፤ በመንግሥታችን ላይ ከፍተኛ ሽብር፤ድንጋጤ እና ፈርሃት አሳደሮ እንደነበረ የትናንትና ታሪክ ነው።

በዚህም ምክንያት የተነሳ፤የመንግሥታችን የስለላና የጸጥታው ክፍል አምነህ ሰፊ ሰራዊት ድምበር ላይ አስቀምጠህ ለበለጠ ጉዳት ስለሚጋለጥ፤ ሠራዊቱ ካንዳንድ ድምበሮች ወደ ኋላ አፈግፍጎ ወደ ሌላ ቦታ እንዲሰፍር የተደረገበት ጊዜ እንደነበር አስታውሳለሁ። በተያያዥ ሁኔታው እጅግ አስፈሪና የማያስተማምን ሆኖ ስለተገመተ፤ አስመራ ውስጥ የነበረው በእኛ ስር የነበረ የአገራዊ ድህንንትና ስለላ ጽ/ቤት ስር የምስጢርና የስለላ ማሕደር/ዶክመንቶች/ አንዳንዱ ወደ ሳሕል ተራራ እንዲዛወር እና እንዲደበቅ ስናደርግ፤ የተቀረው ደግሞ ፤ ታሽጎ ወደ ሌላ ቦታ መቀመጥ ያለባቸው ፋይሎችም

እንደዚሁ እየለየን እንድናሸግና፤ መቃጠል ያለበት ምስጢራዊ ማሕደርም  እንዲቃጠል አድርገናል።

ኢትዮጵያዊያን ከተቆጣጠሩዋቸው ቦታዎች፤ ድንግት ትተውት ከሄዱ በሗላ ግን፤ ወደ ሳሕል አንዲጓዝ ታሽጎ በመጫን ዝግጅት ላይ የነበሩ በርካታ መዛግብቶች፤ ከማጓጓዝ እንዲቆም ተደረገ።   ከዚያ በሗላ፤ የስለላው ደካማነትና ሓላፊነት ለመሸሽ ሲባል፤ ኣስመራ፡ ከረን፡ ባጽዕ፡ መንደፈራ፡ ደቂምሓረ፤ ለስለላ ሥራ ተመድቦ የነበረ አገራዊ የደህንነት ቡድን፤ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች ኤርትራ ውስጥ ለበርካታ አመታት በሰላምና በወንድማማችንት ሲኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያዊያን ወንድሞቻችን፤ ከየቦታው እየለቀሙ “ኮንተይነር” ውስጥ እያሸጉ፤ ለመግለጽ እጅግ በጣም በሚያሰቅቅ ሁኔታ በጅምላዊ ግድያ ወንጀል እንዲፈጽሙ ታዘዙ።

ይህ አሰቃቂ ወንጀል፤ የተፈጸመበት ምክንያት ደግሞ **“አሕያውን ፈርቶ ዳውለውን”** በሰላማዊ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች ላይ እንዲፈጸም ተደረገ። ይህ ወንጀል እንዲፈጸም ደግሞ **በኢሳያስ አፈወርቂ ልዩ ትዕዛዝ እንደተከናወነ**፤ በእነ “**ወልደዝጊ”** እና በእነ **“የማነ ኣፈወርቂ**” አማካይነት በወቅቱ ሰምተነዋል።፡ይህ በምስኪን ኢትዮጵያዊን ንጹሃን ሰዎች የተደረገው የጅምላ ግድያ፤ ብዙ ኤርትራዊ ስለሚያውቀው፤ ጊዜው ሲመጣ አንድ ባንድ ምን፤ ማን፤ እንዴት፤ የት እንደተፈጸመ የሚገለጽ ጉዳይ ነው።

ወያኔ ኤርትራዊያንን ከኢትዮጵያ ሲያባርር፤ ንብረታቸውን ቀምቶ ነበር። ነገር ግን አልገደላቸውም። ለዚያም “የአፈጻጸም ጉድለት ነበር” በማለት ግምገማ በማካሄድ፤ ይፋዊ ይቅርታ በመሪዎቹ በኩል ተጠይቆ፤ ወደ ነበሩበት ተመልሰው በሕጉ መሰረት ንብረታቸው

ተመልሶ በሰላም ንግድ እየነገዱ የሚኖሩ ወይንም ወደ ስራቸው እንዲመለሱ ተደርጋል። ስራቸውና ንብረታቸው እንዲረከቡ ሲፈቀድ፤ ኢሳያስ አፈወርቂ ወደ ኢትዮጵያ አንዳይሄዱ ስላገዳቸው፤ አንዳንዶቹ በምስጢር በሱዳን እና በዱባይ አድርገው ወደ ኢትዮጵያ እየተሻገሩ ንብረታቸው ተረክበው በሰላም እየኖሩ እንዳሉ እዚህ ሆነን በወሬ እንሰማለን። በወሬ ብቻ ሳይሆን በሁኔታው ውስጥ ያሉ ንብረታቸው የተረከቡ ጓደኞቻችን በኩል ተጨባጩ ሁኔታ ይነግሩናል።

በኛ በኩል ግን፤ እነዚያ በንቅዘት የተጨማለቁ ሞራለ ቢስ፤ ወታደራዊ ጀኔራሎችና የመንግሥት ባለስለጣኖች ግን፤ ንጹሃን ኢትዮጵያዊያን በኮንተይነር አፍነው ከገደሉዋቸው በኋላ ንብረታቸው ፤ቤቶቻቸው እየወረሱ ለግላቸው ሲያደርጉት፤ ከሞት የዳኑ ደግሞ፤ ኑሮ አይሉት ሞት ፤ እንደልባቸው እንዳይንቀሳቀሱ እየተከታተሉ በስጋት እንዲኖሩ እየተደረገ ነው። ልዩ የሚያደርገው አሳዛኙ ሁኔታ ደግሞ የተወሰነ “የሰዓት እላፊ” ማዕቀብ ጥለውላቸው፤እንደልብ የማይንቀሳቀሱ፤ በስጋት የሚኖሩ፤ ኑሮአቸው በጣም አሳዛኝ ሆኖ እያየናቸው ነው።

ድሮ ታምር የሆነ፤ የስለላ ስራ ሲሰሩ የነበሩ አስደናቂ የነበሩ፤ ልምድ ያካበቱ፤ የታወቁት የስለላ ባለሞያዎችና ጥበበኞች እስር ቤት ውስጥ በመበስበስ ላይ ያሉት እንደ እነ ጴጥሮስ ሰሎምን የመሳሰሉት ዛሬ ፈልጎ ማግኘት አይቻልም። የስለላ ችሎታ አብሮ ከነሱ ጋር ዘብጥያ ወርዶ ታስሯል። በቃ! ኣበቃ! ዛሬ ያሉት አገራዊ የስለላ ሓላፊዎች፤ ሃይል እየተጠቀሙ ፤ ማሰር ፤ግድያ፤ ማንገላታት እና አመጽ ማካሄድ ካልሆነ ጥበባዊ የስላላ ሥራ የሚሰራ የለም።ሁሉም የነቀዙ፤ የበሰበሱ ናቸው።

4ኛው ነጥብ፤ ዛሬ የኢትዮጵያ የስለላ ሃይሎች የኢሳያስ የስለላ መረብ፤ ተፈታትነውታል ብቻ ሳይሆን ፤ **“ብል”** እንደበላው ልብስ እማሃሉ ውስጥ ገብተው **ቀዳድደውታል**።

የታመኑ እራሱ የመለመላቸው ልዩ ስልጣና የወሰዱ የፕረዚዳንት ኢሳያስ ልዩ “ቦዲ ጋርዶች” ፤አየር ሃይሎችና ባሕር ሃይሎች ከእጁ ተነጥቋል።

የ ቢሻ የወርቅ መአድን ማዕከል የደረሰው ጥቃት አስመልክቶ መንግስታችን አስተያየት ከመስጠት በመቈጠብ፤ “አፍን ዘግቶ” እስካሁን “ዝም” ቢልም።ሰውም ይህንን ጥቃት አስመልከቶ፤ የተለያየ ወሬ ቢናፈስም፤ ጥቃቱ ሲፈጸም ጥበብ እና እጅግ የረቀቀ የስለላ ስራ የተቀናጀ የኢትዮጵያ የስለላ ሃይል እጅ እንዳለበት ሳንግምት አልቀረንም።

በመጨረሻ ልለው የምፈልገው፡ የኤርትራ አገራዊ ደህንነት ፤ በጉልበት፤ በማስፈራራትና በአመጽ ተፈርቶ እንዲኖር የሚፈልግ ካልሆነ በስተቀር ከሕዝብ ጋር እየተቀናጀ አገራዊ ጸጥታ ለማስከበር የማይችል ነው። ባጭሩ እንኳን አገር ሙሉ፤ እራሱን አንኳ ከጥቃት መከላከል የማይችልበት ሁኔታ ሆኖ በንቅዘት የበሰበሰ ክፍል ሆኗል። ተወደደም ተጠላም የኤርትራ አገራዊ ደህንነት ክፍሉ በመሬት ላይ ያለው፤የሚታየው ተጨባጭ እውነታው ከላይ የዘረዘርኩት ነው። በዚህ ቡድን **አገር ትጠፉ እንደሆነ እንጂ ትድናለች ብሎ ማለት** ቅዠት አንደሆነ ደጋግሜ ለማሳሰበብ እወዳለሁ።”

በማለት የድምህት ሊቀመንበር ሞላ አስገዶም፤ ያን ያህል ሰራዊት ይዞ አስቸጋሪ ድምበርና አስቸጋሪ ደረቃማ በረሃ አቋርጦ፤ጥሶ ወደ ሱዳን እና የመሳሰሉ ኢትዮጵያ ድምበሮች ሰራዊቱን ሲያሻግር፤

እንዲያ ዓይነት አስገራሚና አስደናቂ ወታደራዊ የስለላ ክንውንና ሽግግር ሲደረግ፤ የውስጥ ተባባሪ የስለላ ሃይሎች እንዳሉ ከጽሑፉ መረዳት ይቻላል። አሁንም እዘው ያሉ ተቃዋሚ መሪዎች አደገኛ ገመድ አንግታቸው ውስጥ አጥልቀው እየተጓዙ እንዳሉ፤ ሞኞች እና በአጉል ስሜት የተሸፈኑ ሰዎች "ካልሆኑ" በስተቀር ከስሜት ርቀው የስለላና የአካባባው ታሪክ በቂ ግንዛቤ ላላቸው ሰዎች ግን "እጅግ" አደገኛነቱ መገመት አያስቸግርም። እኛ ትግሬዎች **"ዓስ እብለኪ፤ ክር እብለኪ ፤ እንተኣበኽኒ፤ ንነብሪ ይበልኪ**" እንላለን ( ፍየሌ ሆይ፤ **ተይ ተመለሺ፤ ብየ ብመክርሽ፤ እምቢ ካልሺኝ ለአያ ነብሮ/ለነበር ይበልሽ"** ይባላል።

የትግርኛው ደብዳቤ፤ ወደ አማርኛ ተርጉሜ ያቀረብኩላችሁ፤ የ Ethiopian Semay ብሎግ አዘጋጅ፤ ጌታቸው ረዳ ነኝ። አመሰግናለሁ:: getachre@aol.com Monday, October 05/2015